# የሣፅዐቱ የሣሥሩች

ቅፅ 68 ቁጥር 7(811) «እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት + ቀርቦም ሳለ ጥሩት» (ትንቢተ ኢሣይያስ 55 + 6)

## ስለመንፈሳዊ ተሀድሶ የእግዚአብሔር ጥሪ

«በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፣ ፊቴንም ቢፈልጉ፣ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፣ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፣ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ» (2 መዋዕል 7÷14)::

ዛሬ መንፈሳዊ ተሀድሶ ማድረግ የሚገባን ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ ነገር ነው:: ነገር ግን ማነው ለዚህ ተሀድሶ የሚጠራን? ታዋቂ የቤተክርስቲያን መሪ ቢጠራን ጥቂቶች ሊመጡ ይችላሉ፤ የሀገሪቱ መሪ ቢጠሩን ደግሞ መጠኑ የጨመረ ሕዝብ ሊገኝ ይችላል:: የመንፈሳዊ ተሀድሶን ሊጠራ የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ሲሆን ይህም በ2ኛ መዋዕል 7÷14 ላይ ተጠቅሷል:: እግዚአብሔር እራሱ የተሀድሶ ደወሉን አሰምቷል:: አስፈሪው ነገር የስልጣኔ ዕድገት ወደክፋትና ርኩሰት ተለውጦ ፅዋው ሞልቶ እየፈሰሰ ይገኛል:: የኃጢአትና የገሀነም ነበልባል በምድራችን ዙሪያ ሰዎችን እያጠፋ የሚገኝበት ዘመን ላይ እንገኛ ለን::

እግዚአብሔር ለዚህ ወቅት የሚናገረው ቃሉም ይህ 2ኛ መዋዕል 7÷14 ነው:: ችግሩ ያለው ከእግዚአብሔር ድምፅ ሣይሆን ከእኛ ያለማዳመጥ ነው::

### ጥሪው ለማን ነው?

ይህ የተሀድሶ ጥሪ የቀረበው ለእግዚአብሔር ሕዝብ ለክርስቲያኑ ማህበረሰብ ነው:: እግዚአብሔር ሕዝቤ ብሎ የሚጠራው በልጁ በክርስቶስ ደም የገዛው፤ በቅዱስ ጥምቀት ልጅነትን ያገኘውን ሕዝብ ነው:: የእግዚአብሔር ሕዝብ ከፈጣሪው ጋር ተስማምቶ ቢገኝ አንዳች የሚበግረው ነገር አልነበረም::

በትክክል እግዚአብሔር የሚናገረንን እየሰማን ነውን? እኛ እያደረግን ያለነው እግዚአብሔር ፓርላማን ወይንም ሸንጎን እንደሚጠራ ዓይነት ነገር ነው:: የእግዚአብሔር ጥሪ ለፖለቲከኞች ወይንም ለፈላስፋዎች የሚቀርብ ዓይነት አይደለም:: የእግዚአብሔር ጥሪ የሕይወት ጥሪ፤ የፍቅር ጥሪ፤ የትምህርት ጥሪ ነው::

የእግዚአብሔር ሕዝብ የሀገር ችግር መፍትሄ ነው:: የእግዚአብሔር ሕዝብ የሞራልና የሥነ-ምግባር ለውጥ ተምሳሌት ነው:: የእግዚአብሔር ሕዝብ የፍቅርና የእኩልነት ፋና ወጊ ነው:: ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ልጆች አማካኝነት ለጨለመው ዓለም ብርሃን፤ ለታመመው ቤተሰብና ማህበረሰብ መድሀኒት ነው:: የእግዚአብሔር መንፈስ የዓለምን ኃጢአት የሚወቅስ ነው:: (ዮሐንስ 16÷8)

# ጥሪው ምንድን ነው?

ባለሁለት አፍ ሰለትን በመሰለ መልክ የእግዚአብሔር ቃል ቤተክርስቲያንንም ሆነ ዓለምን ይገራል፤ ያርማል:: በበለጠ ግን የእግዚአብሔር ጥሪና መልዕክት ለሕዝቡ እና ለአማኙ ማህበረሰብ ነው:: የእግዚአብሔር ሕዝብ ዛሬ በሀገራችን ኢትዮጵያ ጭምር እራሱን አዋርዶ እግዚአብሔርን መፈለግና ከክፉ መንገድ መመለስ ይገባዋል:: የእግዚአብሔር ዓላማ በተወሰኑ ቅዱሳን ላይ ብቻ ሣይሆን በአጠቃላይ ሕዝቡ ላይና ለዓለም ሁሉ ነውና፤ ዓለም ሁሉ እንዲድን ይወዳልና:: (ዮሐንስ 3÷16)

ዛሬ በዓለም ስላለ ኃጢአትና ርኩሰት ስንናገር በቤተክርስቲያን ካለው ክፋት ለይተን መሆን የለበትም:: ሀገራችን ተሀድሶ እንደሚያስፈልጋት በእጅጉ የታመነ ሲሆን ይህ ተሀድሶ ሲጀመር የሚገባው በቤተመንግስት ሳይሆን በእግዚአብሔር ቤት በክርስትያኑ ማህበረሰብ መካከል ነው::

መንፈስ ቅዱስ የማያምኑትን ክርስቶስን እንዲያምኑ የሚቀሰቅሰውን ያህል አስቀድመው ያመኑትንና የደከሙትን ወደቀደመው ትጋት ይመልሳልና:: አማኞች መንፈስ ቅዱስን ባሳዘኑበት ነገር ንስኃ ገብተው ሲመለሱ የማያምኑት ደግሞ ኃጢአታቸውን በመናዘዝ በክርስቶስ ኢየሱስ ለማመን ይበቃሉ::

ቻርለስ ፊኔ የተባለው የተሀድሶ አስተማሪ እንደተናገረው አማኞች በቤተክርስቲያን ከክፉ ልምዳቸው በንስኃ ሲመለሱ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ የማያምኑትን ልብ እየነካ ወደ ክርስቶስ ማህበር እንዲገቡ ያደርጋል::

ኃጢአተኞችና አመንዝሮች በጥፋታቸው ተፀፅተው ወደክርስቶስ ሲመለሱ የሚያሳዝነው ግን በቤቱ ያሉ በደንዳና ልብ በድፍረት ኃጢአት ሲመላለሱ ነው:: ስለዚህ ዛሬ የመዳን ቀን፣ የንስኃ ቀን፣ የተሀድሶ ቀን ይሁንልን:: (2ቆሮንቶስ 6÷2)

# ተሀድሶ የቤተክርስቲያን ቃል ነው

እኛ በቤተክርስቲያን የምንገኝና የምናገለግል የተለወጠ ሕይወት ሣይኖረን፣ ፍቅርና ምህረት ሣይገኝብን እንዴት ነው ሌሎች እንዲለወጡና ፍቅርን እንዲከተሉ የምንጠብቀው? እኛ በእግዚአብሔር ቤት ተተክልን የምንለው በግብዝነትና በትዕቢት ተሞልተን ሌሎች ትህትና እንዲኖራቸው የምንሰብከው ምን ዓይነት ያለማስተዋል ነው? ኧረ ይብቃን!

እኛ አንዱን ክርስቶስ ጌታን እናምናለን እያልን በጥቃቅን የትርጉም ልዩነት የተለዩንን ከቅዱስ ማህበር የምንገፈትር ምን ዓይነት ጉዶች ነን? እኛ የክርስቶስ ተከታዮች ነን ብለን እርስ በእርሳችን የምንካሰስ፣ የምንወነጃጀል ማን እንዲህ አስተምሮን ይሆን?

ምንድነው እንዲህ ችግር የመጣብን? እንዴት ነው እንዲህ ክርስትና ትርጉሙ የጠፋብን? ቅዱስ ቃሉ እንደሚል ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ይጀምራልና ዛሬ በንስኃ ተስተካክለን የክርስቶስ ልብ ይኑረን! እውነተኛ መንፈሳዊ ተሀድሶም በፍቅርና በምህረት ሕይወት በእኛ እንዲገኝብን ከልብ እንነሣ!

የንስኃ ሥርዓታችን ለዕይታ በጉባዔ ብቻ ሳይሆን እርስ በእርሳችን ይቅር በመባባል አንዳችን የሌላችንን ሸክም እንሸከም:: ያጠፋውንም በፍቅር እንመልስ፤ ተግሣፃችንም ከሕይወት መዝገብ እንገዳ ሣይሆን ወደሕይወት መመለስ ይሁንልን:: እያንዳንዳችን የግንዱ የክርስቶስ ቅርንጫፎች መሆናችንን ተረድተን በእኛ ያለ የክፋት ሥር እንዲወገድ እራሳችንን በየዕለቱ በመመርመር ፍሬ

የሚያበዛውን እና የሚያስተካክለውን ታላቁን ገበሬ ጌታ እግዚአብሔርን እንማፀነው:: (ዮሐንስ 5÷2)

ቤተክርስቲያን የፀሎት ቤት መሆኗን እንደ ክርስቶስ ቃል ተረድተን በቤተክርስቲያን ተገቢውን ልባዊ ፀሎት ለእግዚአብሔር እናቅርብ:: (ማቴዎስ 21÷43)

ሌላው ታላቁ የተሀድሶ አስተማሪ ዶክተር ሙዲ እንዳስተማረው በጌታ ቤት ሥራ የሚካሄደው ለእርሱ በመንበርከክ መሆኑን አውቀን እንስማራበት:: «በአንድ ልብ በጸሎት ይተጉ ነበር» (ሐዋ 1÷7)::

መንፈሳዊ ተሀድሶ ያለስብከት ሊከናወን ቢችልም ያለጸሎት ግን አይሞክርም:: እውርነታችን እንዲበራ ጌታ ዓይናችን ያብራ! ጆሮ ያለው ይስማ የሚለውን የጌታን ቅዱስ ቃሉን ሰምተን ፈፃሚዎች እንድንሆን ያብቃን (ራዕይ 3÷17)::

# መልዕክት ከአሣታሚው
## ሬክ ካርማይክል

## ክርስቶስን በንቃት እንጠብቀው

የክርስቶስ የሆኑ ሁሉ እርሱን በፅናት በመጠበቅ በተሰጣቸው ኃላፊነትና መኽሊት በብርቱ ሲተጉ ይገኛሉ:: (ሉቃስ 19÷13)

እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የሰጠን ኃላፊነትና መኽሊት አለን:: ለእርሱ የምንፈፅመው አገልግሎትና ትጋትም በከንቱ እንደማይቀር በቅዱስ ቃሉ ተስፋ ሠጥቶናል:: (1ኛ ቆሮንቶስ 15÷58)

በክርስቶስ ቤተሰብ የምንሰጠው አገልግሎት የተከበረና የተቆጠረ ሲሆን እርሱ በሚመለስበት ጊዜም ብድራታችንን በሚገባ እንደሚመልስልን ቃሉ ያረጋግጥልናል:: በአገልግሎታችን ተግተን በምንገኝበት ጊዜ የጌታ ማፅናኛ ቃላት የተባረኩና ተስፋን የሚያድሱ ናቸው:: «መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባርያ በጥቂቱ ታምነሀል በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደጌታህ ደስታ ግባ» (ማቴዎስ 25÷21) እግዚአብሔር ብድራትን የማይረሳ፤ ላገለገሉትም ሁሉ ድካማቸውን የማይቆጥር አይደለም:: ይልቁንስ ለእያንዳንዳችን የክብር አክሊል ያዘጋጀ፤ ድካምን የማይረሳ ድንቅ ጌታ እንጅ (ዕብራውያን 6÷7) 2ኛ ጢሞቲዎስ 4÷8)::

የክርስቶስን ዳግም ምፅአት ስንጠብቅ በማንቀላፋትና በስንፍና ሣይሆን በንቃት የክብር አክሊላችንን እንደምንቀበል ታማኝ አገልጋዮች በመሆን ነው:: የክርስቶስ የሆኑት ሁሉ የእርሱን ዳግም መገለጥ ሲጠባበቁ እርስ በእርሳቸው በመፅናናት፣ በመበረታታት ህብረትንም ባለመተው ነው:: (ዕብ10÷24) እርስ በእርሣችን በተስፋና በመበረታታት እንድንገኝ ቃሉ ያሳስበናል:: (ሮሜ 15÷4)

የእግዚአብሔር ቃል ሁለት ስይፍ ያለው የተናጋሪውንም ሆነ የሰሚውን ልብ ሰብሮ የሚገባና ክፋትን ከውስጣችን ቆርጦ የሚጥል ድንቅ ፈውስ

ነው። ስዚህም የክርስቶስ ተከታዮች ዘወትር የተዘጋጁና የሚበረታቱ ሊሆኑ ያሻል።

የክርስቶስ ተከታዮች መታመኛ ከክርስቶስ መንፈስ ውጭ አንዳች ሊሆን አይገባም። ቅዱስ ቃሉ በስጋ ለባሹ የታመነ፣ የተረገመ ይሁን ስለሚል ለጌታ ስራም ሆነ ለዕለት ኑሯችን መታመኛችን ጌታ ብቻ ይሁን።

ያለነቀፋ ሊጠብቀን ለሚችለው ማመንንም፣ ማድረግንም በእኛ ሊፈፅም የሚቻለውን ቅዱስ እግዚአብሔር ዘወትር በጸሎት በመጠየቅ የክርስቶስን ዳግም ምፅአት በንቃት መጠበቅ ይቻላል። «እንግዲህ የነገር ሁሉ መጨረሻ ቀርቧል» (1ጴጥሮስ 4÷7)

# የፀሎት ሕይወታችንን ምን አገኘው?

ዛሬ በየአካባቢው የሚሰማው ነገር የጸሎት ጊዜን የሚያሳስብ ሊሆን ይገባዋል። የክርስቶስ ተከታዮች መታመኛቸው እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ ለሚገጥማቸው ችግርና መከራ ሁሉ ጌታን በጸሎት መጠየቅ ይኖርባቸዋል።

ብዙዎቻችን የወቅቱን ኑሮ፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ ባህልና ልምድ ምክንያት በማድረግ የብርቱ ጸሎት ሕይወታችንን አስነጥቀናል። በጸሎት ስም ስንሰባሰብም ጸሎታችን ከከንፈር ያላለፈ ልብን የማይነካና ለእግዚአብሔር መፍትሄ ፍለጋ ሳይሆን ለፊርማ የሚቀርብ አቤቱታ አስመስለነዋል።

ጌታ የገባልን የተስፋ ቃልን ብንመለከት ግን በተሰበረ ልብ እራሣችንን በማዋረድ ጉድለታችንን በፊቱ ብናፈስ እርሱ እንደሚሰማን ችግራችን እንደሚወገድና ምድራችንም እንደሚፈወስ ነው። (2መዋዕል 7÷14)

ማንኛውም አገልግሎት በክርስቶስ ስም ተደርጐ የልብ ጸሎት ከሌለበት የክርስቶስ መሆኑ የሚያጠራጥርና አደጋ ያለበት ይሆናል። ዛሬ የክርስቶስን ስም ለመጥራት የማይፈልጉ አያሌ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችና ማህበሮች ለዚህ የበቁት ከብርቱ ጸሎት ስለጐደሉ ነው።

አገልግሎታችንና የቤተክርስቲያን ተሣትፏችን ሰው ደስ እንዲለው ይሆን ጌታ ደስ የሚልበትን መፈለግ ትልቅ ማስተዋል ነው። ጌታ በቃሉ እንዳስተማረ መፅሐፍት ሁሉ ወደእርሱ የሚጠቁሙ ስለሆነ አገልግሎታችንም ሁሉ በጸሎት ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የተቆራኘ ሊሆን ይገባዋል።

ትክክለኛዋ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን በስም ብቻ ሳይሆን በቃልና በስራ ክርስቶስ ብቻ የሚሰበክባት የሰው ስራ ሣይሆን የክርስቶስ የመስቀሉ ስራ ብቻ ማዳኑን የምትመሰክር ሊሆን ያሻል። (ኤፌሶን 2÷8)

ወደእግዚአብሔር ቅርቡ እርሱም ወደእናንተ ይቀርባል የሚለው ቅዱስ ቃሉ የሚያረጋግጠው በጸሎትና በቅዱስ ቃሉ ወደእግዚአብሔር ዘወትር መቅረብ እንደሚገባን ለማሳሰብ ነው። (ያዕቆብ 4÷8)

እንግዲህ ዓለም በክርስቶስ መንፈስ ተናውጣ ንስኃ የሚገቡትን ትለቅ ዘንድ እንደሐዋርያቱ ለጸሎት ቅድሚያ ሠጥተን በአንድ ልብ ወደጌታ እግዚአብሔር እንጨህ «ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ሥፍራ ተናወጠ:: በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ»:: (ሐዋርያት 4÷31)

# ዓለምን የሚለውጠው ክርስትና

ክርስቶስን በማመን እንደቃሉ የሚኖር ማህበረሰብ ዓለምን የሚለውጥ ትልቅ የመንፈቅ ቅዱስ ኃይል እንዳለው በዓለም ታሪክ በተደጋጋሚ ታይቷል::

ገና በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ክፍለ ዘመናት የሮማው ቄሣር የዚያን ጊዜው የአውሮፓና የእስያ ገዥ በክርስቶስ ተከታዮች አስደናቂነትና መስዋዕትነት ተስቦ በይፋ ክርስትናን ተቀብሏል::

እውነተኛ ክርስቲያኖች በኖሩባቸው አካባቢዎች ሁሉ ታሪክ እየተቀየረ ክፋትና አመፅ እየተወገደ ስላምና ፍቅር መተካቱን የዓለማችን ታሪክ ይመስክራል::

በአውሮፓ መንፈሳዊ ተሀድሶ በተካሄደባቸው ከተሞች የርኩሰትና የስካር ቦታዎች ሲዘጉ፤ ወንጀልና ሕገወጥ ድርጊት ሲወገዱ ታይተዋል:: «እግዚአብሐር አምላኩ የሚሆንለት ሕዝብ ምስጉን ነው» ንጉስ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም ኃያልም በኃይሉ ብዛት አያመልጥም መዝሙር 32÷12-16.

ክርስቲያኖች ለዚህች ዓለም እንደጌታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን እንዲሆኑ በመጠራታቸው እነርሱ ባሉበት ሁሉ የጨለማ ሥራ ተወግዶ ብርሃናዊ መልካም ሥራ ይተካል:: (ማቴዎስ 5÷14 ዮሐንስ 8÷12)

እግዚአብሔር ገና ከመጀመሪያው በጉኑቱን የገለጠው ዓለምንና መላዋን መልካም አድርጐ ለሰው ዘር ሲፈጥር ነው::

ከዚያም እግዚአብሔር ለመረጠው፣ ለጠራው ሕዝቡ በእምነት አባት አብርሃም በኩል ቃል ኪዳን ሲገባ ዓለምን በመለወጥ ነው:: አብርሃም ከነበረበት ከገዛ ወገኖቹ መንደር ተለይቶ የለውጥ ምሳሌ እንዲሆን በእግዚአብሔር መንገድ እንዲሄድ ከእግዚአብሔር ቃል ተቀብሏል:: (ዘፍጥረት 3÷8 6÷9 17÷1)

ጌታችንና መድኃኒታተን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህች ምድር መጥቶ በሕይወቱ ዋጋ ከፍሎ በመስቀል መከራ ሞትን ተቀብሎ በትንሳኤው ሞትና ሠይጣንን አሸንፎ እኛን ልጆቹ ያደረገን ክፉውን ዓለም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንድንለውጥ ነው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ቅዱስ ቃሉ ዛሬም አልተለወጠም:: በምድራችን፣ በሠፈራችን፣ በከተማችን እና በሀገራችን የተበላሸው፣ የተዛባው እና የከፋው ነገር ወደበጐ እንዲለወጥ ክርስቲያኖች መሣሪያዎች ነን::

የሚለውጠውን ዘላለማዊ ቃሉን ዛሬም እንመገብ በጸሎት ወደጌታ እንቅረብ ተመልሰንም ዓለምን እንለውጥ::

# የሕይወታችን ክንፎች

በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔር በአማኞች ዘንድ ያስቀመጠው ጸጋ ክክፋት፣ ከሞት ከኃጢአትና ከሠይጣን ለማምለጥ የሚረዳ መንፈሳዊ ክንፍ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ቅዱሳን ወይንም አማኞች ይበራሉ የሚለው ምሳሌያዊ አባባል ይህንን በመንፈስ ቅዱስ የሚካሄድ በመንፈሳዊ ክንፍ የመንዝ ልዩ ድርጊት ለማመልከት ነው።

«በርሬ አርፍ ዘንድ እንደ ርግብ ክንፍን ማን በሰጠኝ እነሆ ኮብልዬ በራቅሁ፤ በምድረ በዳም በተቀመጥሁ፤ ከአውሎ ነፋስና ከብርቱ ንፋስ ሸሽቼ በፈጠንሁ አልሁ» (መዝሙር 54÷6) «እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ። እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፣ ይሮጣሉ፣ አይታክቱም ይሄዳሉ። አይደክሙም» (ኢሳይያስ 40÷31)

ገና ከፍጥረቱ እግዚአብሔር በአምሳሉ የሰውን ዘር ሲፈጥር ያስገባበት እስትንፋስ በመንፈስ እንዲበር በክንፎቹ ወደከፍታው የእግዚአብሔር የክብር ሥፍራ እንዲደርስ ነው።

በክንፎቻችን በምንበርበት ጊዜ የዚህን ክፉ ዓለማዊ የፈተና ምድራዊ ጉዟችንን እንገላገላለን። የከበበንም ኃጢአትና አመፅን አልፈን እና ጥለን እንወጣለን።

ትንቢተ ኢሣይያስ መፅሐፉ ለዚህ መንፈሳዊ ክንፍ ብዙ አባባሎችን የዘረዘረ ሲሆን እራሱም ነቢዩ ኢሣይያስ እግዚአብሔርን በዙፋኑ ተቀምጦ ለማየት የበቃውና ነፍሱ የረካችው በመንፈሳዊ መብረር ነው። (ኢሣይያስ 61÷7)

በአዲስ ኪዳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያቱ የተለማመዱትና ያለፉበት ሕይወት በመንፈሳዊ ክንፎች ሆነው ወደእግዚአብሔር ልዩ ከፍታ የደረሱበት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሶስተኛው ሰማይ የገባበት ጴጥሮስና ዮሐንስ ከጌታ ጋር በተራራው ላይ መለኮታዊ መለወጥን ያዩበት የመንፈሳዊ ክንፎች ጉዞ ነው።

ዛሬም አማኞች መንፈሳዊ ክንፍ ያስፈልገናል። በክፋትና በፈታኝ ከበባ በተያዝን ጊዜ ከኃጢአት ጋር ተባብረን ነገ ፀፀትን ከማትረፍ ይልቅ የምናመልጠው በመንፈሳዊ ክንፎቻችን ሀያል እና ፅኑ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በመጥራት በጸሎት በመጋደል ነው።

የእምነት ክንፎቻችን ባለንበት ሥፍራ ሁሉ በኢትዮጵያ ይሁን በአውሮፓ፤ በአሜሪካ ይሁን በአውስትራሊያ፤ በሳዑዲ ይሁን በኢጣሊያ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ያገለግሉናል። ክንፋችን ተመትቶ እያነከስን ከሆነም ዛሬውኑ ወደፈዋሹ ክርስቶስ በጸሎት እንቅረብ እርሱ ያድነናል።

# ልጆቻችንን በሚሲዮናዊ አገልግሎት ስለማሠማራት

«ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም»:: (ምሳሌ 22÷6) ሁላችንም አድገን ለዚህ ደረጃ የበቃነው የልጅነት ዘመናችንን ፈፅመን መሆኑ አይካድም:: በልጅነት ጊዜያችን በአዕምሯችን የተቀረፁና የተማርናቸው ነገሮችም ለቀሪው ሕይወታችን መሠረት ሆነው ይቀራሉ::

ክርስትና ከትውልድ ወደትውልድ በእምነት የሚተላለፍ ሕይወት እንጅ «የእናት እና የአባቴ ሃይማኖት» ተብሎ ለወግ የሚተረክ ጭፍን ልማድ አይደለም::

የማንኛውም ሰው ምኞት ልጆቹ አድገው ለከፍተኛ ደረጃ መብቃት ሲሆን ለክርስቲያኖች ደግሞ ልጆች አድገው በክርስትና እምነት መፅናታቸው ልዩ ደስታችን እና እርካታችን ነው::

ሚሲዮናዊነት ከጥሬ ቃሉ ብንነሳ ሚሽን ወይንም ተልዕኮን መፈፀም ሲሆን ክርስቲያኖች ሁላችንም በተጠመቅንበትና በምናምንበት የክርስትና መርህ መሠረት ዋናው ሚሽናችን ተልዕኳችን የክርስቶስ ኢየሱስ መስካሪነት ነው::

«እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (ሐዋርያት 1÷8)

አዋቂዎችም ሆኑ ልጆች የክርስቶስ ምስክሮች መሆን የምንችለው መጀመሪያ ኃይልና ብርታት፣ እውነትንም የሚገልፅልንን የእግዚአብሔር መንፈስ በመቀበል፣ በመሞላትና በመለኮስ ነው:: የእግዚአብሔርን መንፈስ የምንቀበለው በቅዱስ ጥምቀቱና ከዚያም በኋላ በየጊዜው ቅዱስ ቃሉን በመመገብና በጸሎት በጌታ ፊት በመቆየት ነው:: ከቃሉና ከጸሎት ሕይወት ውጭ የክርስቶስን ተልዕኮ (ሚሽን መፈፀም ከቶ የማይታሰብና የማይቻል ጉዳይ ነው)::

## የክርስቶስን ሚሽን /ተልዕኮ/ ለመፈፀም ጥቂት ምክሮች

1. የክርስቶስ ሚሽን/ተልዕኮን ከመጀመር በፊት ምንነቱን ከመፅሐፍ ቅዱሳችን በተለይም ከሐዋርያ ሥራ እናጥና::
2. የክርስቶስ ሚሽን/ተልዕኮ የግለሰብ ስራ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሆኖ በአማኞች ህብረት የሚገለጥ በመሆኑ ህብረት ይኑረን::
3. የክርስቶስ ሚሽን/ተልዕኮ የሚሣካው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ስለሆነ በቅዱስ ቃሉና በጸሎት ሚሽናችንን/ተልዕኳችንን እንፈፅም::
4. የክርስቶስ ሚሽን/ተልዕኮ ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ የተገባ ነውና አንዳች የግልና የቡድን ዝናና ክብርን ፈፅሞ አንመኝ::
5. የክርስቶህ ሚሽን/ተልዕኮ መሠረት ፍቅር ነውና ሰዎችን ሁሉ በፍቅር እንቀበል::

# ምልጃ ለሌሎች ጉልበት የሚሰጥ የፍቅር አገልግሎት ነው

«የሰጠኸኝን በስምህ እኔ እጠብቃቸው ነበር... እኔም ከአለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም» (ዮሐንስ 17÷12-15)

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አማኝ ልጆቹን እጅግ ስለሚያፈቅረን ምልጃውና ጸሎቱ እኛ ከክፉው ሰይጣን ተጠብቀን እንድንኖር ነው:: አምላካችን ጌታ ኢየሱስ ይህንን የምልጃ ሕይወት ያስተማረንም እኛም በተራችን ለሌሎች ምልጃ በማድረግ ከክፉ እንዲጠበቁና የሕይወት መሠረት የሆነውን እርሱን እንዲቀበሉ ነው::

የምዕአቱ የምሥራች አገልግሎት በዚህ ሁኔታ ለሕዝባችን ደርሶ በሚገባው ቋንቋ ሕዝቡ በመንፈሳዊ መታደስ እምነቱን እንዲጠበቅ የሚመከረው አዘጋጁና ቤተሰቡ ከክፉ እንዲጠበቁ አማኞች ባደረጉት ምልጃ ነው::

ሌሎቹ የምዕአቱ እትሞች ዋናው የእንግሊዝኛው ጭምር በዓለም ዙሪያ ተሠራጭተው ምእመናንን በሕይወታቸው እንዲበረታቱ የሚያደርጉት ወገኖች ለአገልጋዮች ዘወትር በሚያካሂዱት የምልጃ ጸሎት አገልግሎት ነው::

ታላላቆች የእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮችና ሰባኪዎች የሰዎችን ሕይወት የሚለውጥ ስብከትና አገልግሎት የሚሰጡት በአያሌ የምልጃ ጸሎት አገልጋዮች እግዚአብሔር ክንዱን እየገለፀላቸው መሆኑ ሀቅ ነው::
የምልጃ ጸሎት አገልጋዮች ፊት ለፊት የማይታዩ የማይጨበጨብላቸው ስማቸው የማይጠራ ነገር ግን በእግዚአብሔር የከበሩ ታላቁን ሥራውን በዕንባ፣ በፆም እና በጸሎት ቀንና ሌሊት የሚተጉ የእምነት አማኞች ናቸው:: የምልጃ ጸሎት አገልጋዮች አያሌ የእግዚአብሔር ቤት ሠራተኞችን የዚህን ትርጉም አቀናባሪ ጭምር ከሞትና ከመውደቅ እንዲተርፉ ምልጃ ያቀረቡ ናቸው::

የምልጃ ጸሎት ከሁሉ በፊት ለመሪዎች እንዲደረግ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ በላከው መልዕክት ላይ የጠየቀው በመሪዎች ስህተት ሀገር እንደሚፈርስ፤ ሕዝብ እንደሚያልቅ ባለው ትልቅ መረዳት ነው:: (ጢሞ 2÷1)::

ለእግዚአብሔር የሚሳነው አንዳች ነገር የለምና ዛሬም በቤተሰባችን፣ በሠፈራችን፣ በሀገራችን እና በዓለማችን ላይ ለሚታዩት ችግሮችና እንቆቅልሾች ሁሉ ሁላችንም የምልጃ ጸሎት አገልጋዮች ስለሆንን በምልጃችን እንበርታ::

ለዚህ የምዕዐቱ የምሥራች አገልግሎትና ለክርስቶስ የሚሽን/ተልዕኮ ለአቀናባሪውና ለቤተሰቦቹ እንዲሁም ለመላው የሚሽን አገልጋዮች ብርቱ ምልጃ ጸሎት እንዲደረግ በጌታ ፍቅር እንጠይቃለን::

# ዓለም አቀፍ የጸሎት ርዕሶችና ዘገባዎች

## በሕንድ ስለተካሔደው ምርጫ

የሂንዱ ሃይማኖት አክራሪዎች በሕንድ ከሂንዱ ሃይማኖት በስተቀር እንዳይካሄድ የሚተጉበት ፓርቲ በሌላ ከሃይማኖት ነፃ በሆነ ፓርቲ በመሸነፉ ጌታን እናመስግን በሕንድም ሆነ በሌሎች ሀገሮች ክርስትናን የሚያጠቁ አክራሪዎችን መንፈስ በክርስቶስ እንሰበር!

## በካምቦዲያ የሕክምና አገልግሎት

አያሌዎች የክርስቶስን አዳኝነት ባልሰሙበት ካምቦዲያ በክርስቲያኖች የሚካሄደውን የሕክምና አገልግሎት ጌታ ለወንጌሉ መስፋፋት እንዲያውለው እንጸልይ!

## ሙስሊሞችን በቋንቋቸው መድረስ

በራሺያ የሚገኙ ሙስሊሞች በራሣቸው ቋንቋ ወንጌል ስለደረሰላቸው አዳኙ ክርስቶስን በማመን ላይ ናቸው፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያም ጭምር አያሌ ሙስሊሞች በሚገባቸው ቋንቋ በኦሮምኛ፣ በሶማሊኛ እና በአፋርኛ ወንጌል እንዲደርሳቸው ምልጃ እናድርግ፣ ለሥራም እንትጋ!

## የክርስቶስ ሚሽን/ተልዕኮ አገልግሎቶች

ባህላቸውና ቋንቋቸው በተለያዩ ወገኖች ዘንድ የምፅዐቱ ትርጉም አቀናባሪና ቤተሰቡን ጨምሮ የሚያካሂዱት የወንጌል አገልግሎቶች ፍሬ እንዲያፈሩ የምልጃ ጸሎት እናቅርብ፡፡ ይህንን በር ለከፈተ እግዚአብሔር ምልጃ እናቅርብ፡፡

## አጭር የመዳን ምክሮች

1. «በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተም ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ» (ሐዋርያት 16+31)
2. ሕይወታችን እንዲታደስና እንዲስተካከልልን ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር በመናዘዝ ንስኃ እንግባ (ኢሳይያስ 55+7 ሮሜ 3+23 6+23)
3. ለኃጢአታችን መከራ ተቀብሎ በመስቀል የሞተውን በሶስተኛው ቀን ሞትን አሸንፎ በክብር የተነሳውንና በመጨረሻው ቀን በክብር በግርማ የሚመለሰውን ክርስቶስን አምነን እንከተለው ማርቆስ (10+33) (ዮሐንስ 1+12) በየቀኑም እንታደስ፣ እንፅና፡፡ ሮሜ 12+2

# ልዩ ማሳሰቢያ ለአንባቢዎች

በየጊዜው ስለምትገልፁልን ምስጋና እና ለምትልኩልን ልባዊ ድጋፍ ጌታ የተመሰገነ ይሁን!
ሁላችሁንም ከልብ እናመሰግናለን። ለአገልግሎቱ መቀጠል አሁንም
የሚቻላችሁን የጸሎትና የገንዘብ ድጋፍ በተጠሪዋ
በወ/ሮ አልማዝ አሳየ በኩል እንድትልኩ
በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም
እንጠይቃችኋለን።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው!
አደፍርስ ሀብቴ መካሻ
ሴንት ሉዊስ
አሜሪካ

## የምፅዐቱ የምሥራች የወንጌል አገልግሎት

| ትርጉምና ቅንብር | አርትኦትና ዲዛይን | በኢትዮጵያ ተጠሪ |
|---|---|---|
| አደፍርስ ሀብቴ መካሻ | ኤልሣቤጥ ባስልዮስ | አልማዝ አሣዬ |
| ሴንት ሉዊስ | አዲስ አበባ | የመ.ሣ.ቁ 8986 |
| አሜሪካ | ኢትዮጵያ | አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ |